# ሊባኖስ፡- የቤት ሠራተኞች ላይ የሚፈጸመው በደልና ጥቃት ይቁም

***በቅርቡ የተፈጸመው ራስን የማጥፋት ድርጊት ላይ ምርመራ ይካሄድ፤ለሠራተኞችና ለስደተኞች ጥበቃ የሚያደርግ ሕግ ይውጣ***

(ቤይሩት፣ መጋቢት 14 ቀን 2004 ዓ.ም.) - ከውጭ ሀገራት በሚመጡ የቤት ሠራተኞች ላይ የሚፈጸመውን እጅግ የከፋ በደልና ሞት ለማስቀረት እንዲቻል የሊባኖስ ባለስልጣናት በአፋጣኝ በመንቀሳቀስ ጥብቅ የሆኑትን ቪዛን የሚመለከቱ ደንቦች ማሻሻልና የቤት ሠራተኞችን የሚመለከት የሠራተኛ ሕግ ማውጣት ይኖርባቸዋል ሲሉ ጉዳዩ ያሳሰባቸው ስምንት የሲቪል ማህበራት ዛሬ አሳሰቡ። ከዚህ በተጨማሪም መንግስት በቅርቡ የተፈጸመባትን በደልና ጥቃት ተከትሎ ሕይወቷን ስላጠፋችው ኢትዮጵያዊት የቤት ሠራተኛ ዓለም ደቻሳ ደሲሳ ያካሄደውን ምርመራ ውጤት ይፋ ማድረግ አለበት።

ስምንቱ የሲቪል ማህበራት፡ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ካሪታስ ሊባኖስ የስደተኞች ማዕከል፣ካፋ (በቃ) ጥቃትና ብዝበዛ፣የፀረ ዘረኝነት ንቅናቄ፣ዐመል ዓለማቀፍ ማህበር፣ኢንሳን፣የዴኒሽ ስደተኞች ምክር ቤት እና ናሳዊያ ናቸው።

የካቲት 29 ቀን 2004 ዓ.ም. ኤልቢሲአይ የተባለ የሊባኖስ ቴሌቪዥን ጣቢያ ማንነቱ ባልተገለጸ ሰው የካቲት 16 ቀን 2004 ዓ.ም. የተቀረጸ ቪዲዮ ይፋ አድርጓል። ይህ ቪዲዮ አንድ የሥራ አስቀጣሪ ዓለም ደቻሳን ቤይሩት ከሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት አጠገብ አካላዊ ጥቃት ሲፈጽምባት የሚያሳይ ነው። ቪዲዮው በተጨማሪም ሥራ አስቀጣሪውና ሌላ ግለሰብ ዓለምን በግዳጅ ወደመኪና ለማስገባት ሲጎትቷት ያሳያል። ቴሌቪዥን ጣቢያው በኋላ ድብደባውን ሲፈጽም የሚታየው ግለሰብ አሊ ማህፉዝ እንደሚባልና ግለሰቡም ዓለም ደቻሳን ወደ ሊባኖስ ያመጣት ሥራ አስቀጣሪ ኤጀንሲ ሃላፊ ወንድም እንደሆነ ይፋ አድርጓል። አሊ ማህፉዝ በቴሌቪዥን ቃለ መጠይቅ የተደረገለት ሲሆን በዚህ ጊዜም ዓለም የአእምሮ መታወክ ችግር የነበረባት በመሆኑ የወንድሙ ኤጀንሲ ዓለምን ወደ ሀገሯ ለመመለስ ሲሞክር እንደነበር ገልጿል።

ፖሊሶች በአጭር ጊዜ ውስጥ በስፍራው የደረሱ ሲሆን መኪናውንም እዚያው ለማግኘት ችለዋል፤ ከዚያም በስደተኞች (አስሮ) ማቆያ ጣቢያ ተወካይ ያለው ካሪታስ ሊባኖስ የስደተኞች ማዕከል ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ዓለም ደቻሳን ወደ ማቆያ ጣቢያ ወስደዋታል። ከሁለት ቀናት በኋላ ወደ ሕክምና ማዕከል ያዛወሯት ሲሆን ድብደባውን የፈጸሙባትን ሰዎች ግን በቁጥጥር ስር አላዋሉም። ዓለም ደቻሳ ዳኢር አል ሳሊብ የስነ አዕምሮ ሆስፒታል ውስጥ መጋቢት 5 ቀን 2004 ዓ.ም. ማለዳ ላይ ሕይወቷን በገዛ እጇ አጥፍታለች። ዓለም ደቻሳን ዳኢር አል ሳሊብ ሆስፒታል በመገኘት የጎበኙት የካሪታስ ሊባኖስ የስደተኞች ማዕከል የማህበራዊ ጉዳይ ሠራተኛ ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደገለጸችው አንድ ሊባኖሳዊ የወንጀል ጉዳዮች መርማሪ ሀኪም ዓለም ደቻሳን መጋቢት 1 ቀን መርምሯት ነበር።

የሂዩማን ራይትስ ዎች የመካከለኛው ምስራቅ እና የሰሜን አፍሪካ ምክትል ዳይሬክተር ናዲም ሃውሪ እንዳሉት "የዓለም ደቻሳ ሞት ሁለት ደረጃ ያለው ጥፋት ነው፡ የደረሰባት የሃይል ጥቃትና ይህን መሰሉን አሳዛኝ ክስተት ለመከላከል የሚያስችል (ሕጋዊ) ጥበቃ አለመኖር። መንግስት በሀገሪቱ ውስጥ በቤት ሠራተኞች ላይ በስፋት የሚፈጸመውን በደል ለማስቆምና የሚደርሰውን የሞት መጠን ለመቀነስ የሚያስችል ከረጅም ጊዜ በፊት ማውጣት የነበረበትን ጥበቃ በሕግ መልክ ማጽደቅ ይኖርበታል።"

የቪዲዮውን በስፋት መሰራጨት ተከትሎ ዓለም ደቻሳ ላይ በተፈጸመው ድብደባና ማንገላታት ላይ ምርመራ እንደሚያደርጉ የሠራተኛ እና የፍትሕ ሚኒስትሮች መጋቢት 1 ቀን አስታውቀው ነበር። የምርመራው ውጤት እስካሁን ይፋ ያልተደረገ ሲሆን ዐቃቤ ሕግም በአሊ ማህፉዝ ላይ የወንጀል ክስ ለመመስረት ስለማሰቡ የሚታወቅ ነገር የለም።የሥራ አስቀጣሪ ኤጀንሲዎችን የሚቆጣጠረው የሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር በአሊ ማህፉዝ ኤጀንሲ ላይ የተወሰደ እርምጃ ስለመኖሩ ያቀረበው ሪፖርት የለም።

"የሊባኖስ ባለስልጣናት ምርመራ የጀመሩት የመገናኛ ብዙሃን ትኩረት ስላረፈባቸው ብቻ ነው።" የሚሉት ሃውሪ "መንግስት ከውጭ ሀገራት የሚመጡ በርካታ የቤት ሠራተኞችን ወደ ተስፋ መቁረጥ ለሚገፏቸው መሠረታዊ ምክንያቶች በአስቸኳይ መፍትሔ ሊያበጅ ይገባዋል።" በማለት አሳስበዋል።

እ.ኤ.አ በ 2008 ሂዩማን ራይትስ ዎች ሊባኖስ ውስጥ ከሌሎች ሀገራት የመጡ የቤት ሠራተኞችን ሞት አስመልክቶ መረጃዎችን አጠናቅሮ ነበር። በዚህም መሠረት ራስን ማጥፋትንና ከረጅም ሕንጻዎች ላይ መውደቅን ጨምሮ ተፈጥሮአዊ ባልሆኑ ምክንያቶች በአማካይ በሳምንት አንድ ሞት ተመዝግቦአል። ካፋ (በቃ) ጥቃትና ብዝበዛ የተባለው የሊባኖስ የሴቶች መብት ደርጅት እ.ኤ.አ. በነሀሴ ወር 2010 ብቻ ዘጠኝ የሞት አደጋዎችን የሚመለከቱ መረጃዎችን አሰባስቦአል። ካሪታስ ሊባኖስ የስደተኞች ማዕከል እንደሚገልጸው ደግሞ በአሁኑ ጊዜ አምስት ኢትዮጵያውያን የቤት ሠራተኞች በዳኢር አል ሳሊብ የስነአዕምሮ ሆስፒታል ውሰጥ የሚገኙ ሲሆን እነሱም ከጠቅላይ የደህንነት ማቆያ ጣቢያ የተዛወሩ ናቸው።

ሊባኖሳውያን ቤተሰቦች በዋናነት ከሲሪ ላንካ፣ ከኢትዮጵያ፣ ከፊሊፒንስ እና ከኔፓል የመጡ በግምት 200,000 ሺህ የሚሆኑ የቤት ሠራተኞችን ቀጥረው ያሰራሉ። የሀገሪቱ የአሰሪና ሠራተኛ ሕግ በቤት ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚነት የሌለው ሲሆን እነዚህ ሠራተኞች ለብዝበዛ በሚያጋልጡና ስፖንሰር በሚያደርጓቸው ቀጣሪዎቻቸው ፍላጎት መሠረት በሚወሰኑ ጥብቅ በሆኑ የኢሚግሬሽን ደንቦች የሚተዳደሩ ናቸው። ደንቦቹ በተጨማሪም ሠራተኞቹ በደል የሚያደርሱ ቀጣሪዎችን ትተው እንዳይሄዱ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ናቸው። የሚፈጸሙት በደሎች ስፋት ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ ሀገራት ዜጎቻቸውን ሊባኖስ ሄደው መስራትን እንዲከለክሉ አድርጓቸዋል። ወደ ሊባኖስ በሚደረገው ይፋዊ ጉዞ ላይ የተጣለው ክልከላ ግን የቤት ሠራተኞችን ወደዚያ ከመፍለስ አላገዳቸውም፤ እገዳው ምናልባትም ሴቶቹ በሕገወጥ መንገድ እንዲጓጓዙና ወደ ሊባኖስ እንዲገቡ አስተዋጽኦ ሳያደርግ አይቀርም።

ሠራተኞችን ወደሊባኖስ በሚልኩ ሀገራት ኤምባሲዎችና በሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ከተሰባሰቡ በጣም ተደጋጋሚ በደሎች ውስጥ በአስቀጣሪዎች የሚፈጸም ማንገላታት፣ደመወዝ አለመክፈል ወይም ማዘግየት፣ሠራተኞችን በሥራ ቦታቸው አስገድዶ ማቆየት፣ ዕረፍት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን በሃይል አስገድዶ ማሰራት እንዲሁም ስድብና አካላዊ ጥቃት ማድረስ ይገኙባቸዋል።የሊባኖስ ባለስልጣናት የቤት ሠራተኞችን የሥራ ሁኔታ እንደሚያሻሽሉ ተደጋጋሚ መግለጫዎችን የሰጡ ቢሆንም  የተደረጉት ለውጦች ግን ውሱን ናቸው። እ.ኤ.አ. በጥር ወር 2009 አስገዳጅነት ያለውና ወጥ የሆነ የቅጥር ውል ሥራ ላይ የዋለ ቢሆንም ይህ ውል ግን በአረብኛ ቋንቋ ብቻ የሚገኝና ዋናው የአሰሪና ሠራተኛ ሕግ ለሌሎች ሠራተኞች ከሚሰጠው ጋር ሲነጻጸር እጅግ ደካማ የሆኑ ጥበቃዎችን የያዘ ነው።

የቤት ሠራተኞችን የኑሮና የሥራ ሁኔታ የሚገዛ አዲስ ሕግ ለማውጣት የተደረጉ ጥረቶች ብዙም ሳይገፉባቸው ቀርተዋል። እ.ኤ.አ. በየካቲት 2011 የሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቡትሮስ ሃርብ አሁን የሚሰራበትን “ከፈላ” የሚሰኘውን የስፖንሰርሺፕ ስርዓት ባለበት የሚያቆይ የቤት ሠራተኞችን የሥራ ሁኔታ የሚገዛ የሕግ ረቂቅ አቅርበው የነበረ ቢሆንም በተደረገው የመንግስት ለውጥ ምክንያት ረቂቁ የትም ሳይደርስ ተትቷል። ጥር 14 ቀን 2004 ዓ.ም. አዲሱ የሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስትር ቻርቤል ናሃስ “ከፈላ” የተሰኘውን አሰራር እንደሚያስቀሩ በይፋ ገልጸው ነበር፤ ይሁንና ሚኒስትሩ ከዚህ ጋር ባልተያያዘ ምክንያት ከአንድ ወር በኋላ ስልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለቀዋል። አዲስ የተሾሙት የሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስትር ሳሊም ጅሬይሳቲ የቤት ሠራተኞች ላይ በስፋት የሚፈጸመውን በደል ለማስቆም ያላቸውን ዕቅድ አስመልክቶ እስካሁን የገለጹት ነገር የለም።

ሃውሪ እንደሚሉት “የቤት ሠራተኞች በሕግ የተደነገጉ መብቶች የሌሏቸው መሆኑና ጥብቅ የሆኑ ቪዛን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች መኖር የቤት ሠራተኞችን ለመገለል፣ ለእንግልት፤ ለዕዳና በደልን ሸሽተው እንዳያመልጡ ለማድረግ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው።” “መንግስት የስፖንሰርሺፕ አሰራርን ቅድሚያ ሰጥቶ ማሻሻልና ከዓለማቀፍ መመዘኛዎች ጋር የሚጣጣም  የቤት ውስጥ ሥራን የሚመለከት ሕግ ማውጣት አለበት።”

ዓለማቀፉ የሥራ ድርጅት እ.ኤ.አ. ሰኔ ወር 2011 ያጸደቀውን ለቤት ሠራተኞች ተገቢ የሥራ ሁኔታን መፍጠርን የሚመለከተውን ስምምነት ቁጥር 189 ሊባኖስ በመደገፍ ድምጽ ሰጥታለች። ይሁንና እስካሁን ድረስ ስምምነቱን አላጸደቀችም ወይም ለስምምነቱ ተገዢ አልሆነችም። ይህ የዓለማቀፉ የሥራ ድርጅት ስምምነት በመላው ዓለም ቁጥራቸው ከ 50 ሚሊዮን እስከ 100 ሚሊዮን እንደሚደርስ የሚገመተውን  የቤት ሠራተኞች  አስመልክቶ  የመጀመሪያውን  ዓለማቀፍ መመዘኛዎች ያካተተ ስምምነት ነው። የስምምነቱ ዋና ዋና ክፍሎች መንግስታትን ለሌሎች ሠራተኞች የሚሰጡትን ሕጋዊ ጥበቃ ለቤት ሠራተኞችም እንዲሰጡ፣ አስቀጣሪ ኤጀንሲዎችን በጥብቅ እንዲከታተሉ እንዲሁም ጥቃቶች እንዳይፈጸሙ ጥበቃ  እንዲያደርጉ የሚጠይቁ ናቸው።

በቤት ሠራተኞች ላይ በደል የሚፈጽሙ ሰዎችን በመቅጣት ረገድ ሊባኖስ ያለችበት ደረጃ ደካማ ነው። እ.ኤ.አ በ 2010 “Without Protection: How the Lebanese Justice System Fails Migrant Domestic Workers” በሚል ርዕስ የወጣው የሂዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርት ከሌሎች ሀገራት የመጡ የቤት ሠራተኞችን የሚመለከቱ 114 በፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎችን የመረመረ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የቤት ሠራተኛ ላይ ቤት በቆለፈ፣ፓስፖርት ነጥቆ በወሰደ ወይም ምግብ በከለከለ አንድም ቀጣሪ ላይ ክስ አልተመሰረተም።

በ 13 የወንጀል ጉዳዮች ላይ የተደረገው ጥናትም ለአንድ ጉዳይ እልባት ለመስጠት በአማካይ 24 ወራትን እንደፈጀ ያሳየ ሲሆን ከሶቹም በቀላል ቅጣት እንደተቋጩ አሳይቶአል። ሂዩማን ራይትስ ዎች የሚያውቀው የቤት ሠራተኛን ለመደብደብ ወንጀል የተሰጠው የመጨረሻው ከባድ ቅጣት ሲሪላንካዊት የቤት ሠራተኛውን በተደጋጋሚ በደበደበው አሰሪ ላይ  ሰኔ 19 ቀን 2002 ዓ.ም. በወንጀል ፍርድ ቤት የተሰጠው የአንድ ወር እስራት ነው።

ሃውሪ እንደሚሉት “የሊባኖስ ባለስልጣናት የዓለም ደቻሳን አሟሟት የተለያዩ ገጽታዎች ማለትም ሲፈጸም በቪዲዮ የተቀረጸውን ጥቃት፣ ቪዲዮው ከመሰራጨቱ በፊት ፖሊስ በጥቃቱ ላይ ለምን ምርመራ እንዳላካሄደ እንዲሁም ሆስፒታል ውስጥ እያለች ሕይወቷ ያለፈበትን ሁኔታ መመርመር አለባቸው። በተጨማሪም መንግስት የቤት ሠራተኞች በደል ሲፈጸምባቸው ሪፖርት ለማድረግ

የሚችሉበትን ሁኔታ ለማሻሻል የሚያስችል ብሔራዊ ዕቅድ ማውጣት እንዲሁም ለፖሊስ፣ለኢሚግሬሽን ሠራተኞች እና ለዳኞች  የዚህ ዓይነት ጉዳዮችን በተሻለ ሁኔታ ለማስተናገድ የሚያስችላቸውን ስልጠና መስጠት አለበት።"

**"Without Protection: How the Lebanese Justice System Fails Migrant Domestic Workers" የሚለው የሂዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርት በ http://www.hrw.org/node/93006  ይገኛል።**

**ካሪታስ ሊባኖስ የስደተኞች ማዕከል ስለ ዓለም ደቻሳ ጉዳይ ያወጣው ዘገባ በ http://emglish.caritasmigrant.org.lb/?p=1335**

**የቤት ሠራተኞችን የሚመለከቱ ተጨማሪ የሂዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርቶችን ለማግኘት http://www.hrw.org/topic/womens-rights/domestic-workers  ይጎብኙ።**

**ለተጨማሪ መረጃ፡**

ቤይሩት፦ ናዲም ሃውሪ (አረብኛ፣እንግሊዝኛ፣ፈረንሳይኛ)፡ +961-3-639244 (ሞባይል)፣ ወይም houryn@hrw.or

ኒው ዮርክ፦ ኒሻ ቫሪያ (እንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽ)፡ +1-917-617-1041 (ሞባይል)፣ ወይም varian@hrw.org

ኒው ዮርክ፦ ዳንኤል በቀለ (እንግሊዝኛ፣ አማርኛ)፡ +1-212-216-1223፣ +1-917-385-3878 (ሞባይል)፣ ወይም  bekeled@hrw.org

**ስለ ዓለም ደቻሳ ደሲሳ**

ዓለም ደቻሳ ደሲሳ ቡራዩ ከተሰኘ የአዲስ አበባ አካባቢ የመጣች የ33 ዓመት ኢትዮጵያዊት ስትሆን ሁለት ልጆችም ነበሯት። ወደ ሊባኖስ የሄደችው በታህሳስ ወር 2004 ሲሆን  በአንድ የሊባኖስ ሥራ አስቀጣሪ ኤጀንሲ በኩል ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ዜጎቹ ወደ ሊባኖስ ሄደው እንዳይሰሩ እገዳ የጣለ በመሆኑ ወደ ሊባኖስ የሄደችበት ሁኔታ ትክክለኛውን መንገድ የተከተለ አልነበረም።

ዓለም ደቻሳ የካቲት 16 ቀን 2004 ወደ ጠቅላይ ደህንነት የማቆያ ጣቢያ ተወስዳ ከታሰረች በኋላ ጉዳይዋን መከታተል የጀመረችው የካሪታስ ሊባኖስ የስደተኞች ማዕከል የማህበራዊ ጉዳይ ሠራተኛ እንደገለጸችው ዓለም በመጀመሪያ ለአንድ የሊባኖስ ቤተሰብ ለአንድ ወር ከሰራች በኋላ የመግባባት ችግር በመፈጠሩ ወደ ኤጀንሲው እንድትመለስ ተደርጓል። ለሰራችበት አንድ ወር ደመወዝ አልተከፈላትም። ለሌላ አሰሪ ለጥቂት ቀናት የሰራች ቢሆንም ይህም አሰሪ ወደኤጀንሲዋ መልሷታል።

ሁለተኛው አሰሪ ከሥራ ካባረራት በኋላ አስቀጣሪው ኤጀንት የደበደባት መሆኑንና ወደ ኢትዮጵያ መልሶ እንደሚልካት በመግለጽ አስፈራርቷት እነደነበር ዓለም ለማህበራዊ ጉዳይ ሠራተኛዋ ነግራታለች። ወደ ሊባኖስ ለመምጣት ኢትዮጵያ የገባቻቸውን ዕዳዎች ለመክፈል እና ለቤተሰቦቿም ለመላክ ገንዘብ ማግኘት ያስፈልጋት እንደነበርም ተናግራለች። ኤጀንቱ ሁለት ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ሊመልሳት አውሮፕላን ጣቢያ ወሰዷት እንደነበርና አልሄድም በማለት አውሮፕላን  ጣቢያ ውስጥ መጮኋን የገለጸች ሲሆን ከአውሮፕላን ጣቢያው ወደ ኤጀንሲው ከተመለሰች በኋላ ክሎሮክስ በመጠጣት ራሷን ለመግደል ሙከራ አድርጋ እንደነበር ተናግራለች። ኤጀንሲው እንደሚለውም ከመኪና ዘላ በመውረድ ለሁለተኛ  ጊዜ ራሷን ለማጥፋት ሞክራለች።

የካቲት 16 ቀን አስቀጣሪ ኤጀንቱ ዓለምን ወደ ኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት ወስዶ የአዕምሮ ችግር ያለባት መሆኑን በመግለጽ እዚያው ትቷት መሄድ ይችል እንደሆነ ጠይቋል። የቆንስላ ጽ/ቤቱን የሥራ ሃላፊ ያነጋገረ አንድ ሊባኖሳዊ የሙብት ተሟጋች ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደገለጸው ቆንስላ ጽ/ቤቱ  ጥያቄውን ባለመቀበል ወደ አዕምሮ ሕክምና ሆስፒታል እንዲወስዷት ነግሯቸዋል። ከዚያም ኤጀንቱ ከሌላ ግብረ አበሩ ጋር በመሆን በዓለም ደቻሳ ላይ አካላዊ ጥቃት ሲፈጽሙ እና ወደ መኪናው እንድትገባ ሲያስገድዷት ታይተዋል። ሁኔታውን ሲመለከት በነበረ አንድ ግለሰብ በቪዲዮ ተቀርጾ ከሁለት ሳምንታት በኋላ በኢንተርኔት የተሰራጨውም ይኸው ክስተት ነው።

በቪዲዮው የሚታየው ድርጊት ከተፈጸመ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ፖሊሶች በስፍራው በመድረስ ዓለም ደቻሳን ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከዚያም ተገዳ ወደሀገሯ እንድትመለስ ወደ ጠቅላይ ደህንነት ማቆያ ጣቢያ ወስደዋታል። ዓለም ደቻሳ የአዕምሮ መነካት ምልክቶች ታሳይ እንደነበር፣ ያለማቋረጥ ታለቅስ  እንደነበርና በሚቀጥለው ቀንም ወደ ናውፋል ሆስፒታል የተወሰደች መሆኑን የዓይን ምስክሮች

ለሂዩማን ራይትስ ዎች ገልጸዋል። ሁኔታዋ መሻሻል ባለማሳየቱ የካቲት 23 ቀን ወደ ዳኢር አል ሳሊብ የስነ አዕምሮ ሕክምና ሆስፒታል ተዛውራለች።

የቪዲዮውን መሰራጨት ተከትሎ የካቲት 29 ቀን ሕዝባዊ ቁጣ ተቀስቅሶ ነበር። ከዚያም ዐቃቤ ሕግ ምርመራ ጀመረ። መጋቢት 1 ቀን የወንጀል ጉዳዮች መርማሪ ሃኪም እና የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት ተወካይ ዓለምን ለመጀመሪያ ጊዜ በዳኢር አል ሳሊብ ሆስፒታል በመገኘት ጎብኝተዋታል። የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት በዓለም ስም ክስ የመሰረተ መሆኑን አስታውቋል። መጋቢት 5 ቀን ዓለም ደቻሳ ራሷን በአንሶላ በማነቅ ሕይወቷን አጥፍታለች ተብሏል።